# Arlington Public Schools
# የተማሪዎች ድጋፍ መስጫ ሒደት

Arlington Public Schools (APS) ተማሪዎችን የሚደግፍበት ጠንካራ ሒደት አለው። የቤተሰብ ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበን ዋጋም እንሰጣለን፤ እርስዎም ስለ ተማሪዎች ድጋፍ መስጫ ሒደት የሚያውቁ መሆንዎትንና የልጅዎን አካዳሚክ፣ ማህበረ-ስሜታዊ እና/ወይም ባህርያዊ ፍላጎቶችን በተመለከተ የሚያሳስቡዎት ጉዳዮች ቢኖሩ ከልጅዎ ት/ቤት ጋር አጋርነት መፍጠር የሚችሉባቸውን መንገዶች ማወቅዎን ለማረጋገጥ እንፈልጋለን። ሰራተኞች ተማሪዎችን በተመለከተ የሚያሳስባቸው ጉዳይ ሲኖር የሚከተሉት ሒደት ከዚህ በታች ቀርቧል።

## ደረጃ 1

**መምህር**



**<u>የተማሪ ድጋፍ መስጫ ሒደት ደረጃ 1</u>**

የአንድን ተማሪ አካዳሚክ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ወይም ባህርያዊ ሁኔታን በተመለከተ አሳሳቢ ጉዳይ ቢኖር፣ መምህሩ ጉዳዩን ለቤተሰብ በማሳወቅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ድጋፎችን ማድረግ እንደሚጀምር ይጠበቃል። መምህሩ ዳታ በመጠቀም የተለያየ የማስተማር ዘዴን ይሰጣሉ፣ ድጋፍን ይተገብራሉ፣ እምርታን ይከታተላሉ፣ ቀጣይ እርምጃ መወሰድ ካለበትም ምን እንደሚሆን ይወስናሉ።

## ደረጃ 2

**የትብብር ትምህርት/የመምህር ቡድን (CLT)**



**<u>የተማሪ ድጋፍ መስጫ ሒደት ደረጃ 2</u>**

አንድ ተማሪ አሁን እያገኘ ባለው ድጋፍ አማካይነት የሚጠበቅበትን እምርታ ካላሳየ፣ መምህሩ በት/ቤቱ ውስጥ ለሚገኙ ተባባሪ ሰራተኞች ቡድን ጉዳዩን በማሳወቅ ተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብና ተጨማሪ እርምጃዎችንም ለመፈተሽ ከተማሪው ቤተሰብ ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ። ቡድኑ እምርታን በመከታተል ቀጣይ እርምጃዎች መወሰድ ካለባቸው ምን ዓይነት ይሁን የሚለውን ይወስናል። ቡድኑ የሚወሰደውን እርምጃ ሊቀጥል፣ሊከልስ ወይም ወደ ተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን ለማስተላለፍ ሊወስን ይችላል።

## ደረጃ 3

**የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን (SST)**

- የጣልቃ ገብነት ዕቅድ
- የልዩ ትምህርት ምዘናዎች
- የክፍል 504 ማጣሪያ



**<u>የተማሪ ድጋፍ መስጫ ሒደት ደረጃ 3</u>**

እርምጃዎች በታማኝነት ቢያንስ ለ5-6 ሳምንታት ከተወሰዱ በኋላ ተማሪው የሚጠበቅበትን እምርታ ሊያሳይ ካልቻለ፣ መምህሩ ወደ ተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን (SST) እንዲተላለፍ ያደርገዋል፤ ይህ ቡድን በእያንዳንዱ ት/ቤት ውስጥ የሚገኝና ከተለያየ ሙያ የተውጣጡ አባላት ያሉት ሲሆን በቡድኑ ውስጥም ወላጆች/አሳዳጊዎች ያሉበት ሆኖ የሚመራውም በተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ (SSC) ነው። SST ሪፈራሎችን ይገመግማል፣ ከተወሰዱ እርምጃዎች የተሰበሰበ ዳታን ይተነትናል፣ ቀጣይ እርምጃዎችም ይወስናል፤ በዚህም ውስጥ ይበልጥ መደበኛ የሆነ የጣልቃ ገብነት ዕቅድ፣ እና/ወይም ወደ ልዩ ትምህርት ምዘና ወይም የአንቀጽ 504 ማጣሪያ መተላለፍ ሊካተት ይችላል።

Arlington Public Schools

ወላጆች/አሳዳጊዎችም የድጋፍ ቡድን ሒደትን ማስጀመር ይችላሉ። የልጅዎን አካዳሚክ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ዕድገት ወይም ባህርይ በተመለከተ የሚያሳስቡዎት ጉዳዮች ካሉ፣ መውሰድ ያለብዎት የመጀመሪያው እርምጃ ከልጅዎ መምህር(መምህራን) ጋር በቀጥታ በመነጋገር ያሳሰበዎትን ጉዳይ ማጋራት ነው። በተጨማሪም፣ የአካል ጉዳት መኖሩ ከተጠረጠረ የልዩ ትምህርት እና/ወይም የክፍል 504 ብቁነት ላይ ማጣራት ለማድረግ የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን ስብሰባ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ። ወላጆች ጥያቄ ሲኖራቸው እና/ወይም ተጨማሪ መረጃ ለመቀበል ለወላጆች የመረጃ ማዕከል በኢሜይል prc@apsva.us ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-7239 ማሳወቅ ይችላሉ።